## መመሪያ ቁጥር 813/2013
## ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች ዝርዝር እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ

### መግቢያ

ወጣት ሠራተኞች በሥራ ላይ ሲሰማሩ ለተለያዩ የሥራ ላይ አደጋዎች ፣ የጤና ጉዳቶች በተለይ ከባድ ከሆኑ የጤና ጉዳት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ጠንቆች እና አደገኛ የስራ ሁኔታዎች ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

1. **<u>አውጪው ባለስልጣን</u>**

   የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 89(4) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ መመሪያ "ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች ዝርዝር እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 813/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **<u>ትርጓሜ</u>**

   በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

   1. **"አዋጅ"** ማለት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ማለት ነው፡፡
   2. **"ወጣት ሠራተኛ "** ማለት ዕድሜው 15 ዓመት

## Directive No 813/2021
## Directive on the Restating of Activities Prohibited for Young Workers

### Introduction

This Directive has been issued in order to protect young workers from serious occupational injuries or damages to their health from in the course of their work.

1. **<u>Legislating Authority</u>**

   The Ministry of Labor and Social Affairs has issued this Directive in accordance with the authority vested on it by Labor Proclamation No. 1156/2011 Article 89/4/.

2. **<u>Short Title</u>**

   This Directive may be cited as "Directive on the Restating of Activities Prohibited for Young Workers" Directive No 813/2021.

3. **<u>Definitions</u>**

   For the implementation of this Directive:

   1) **''Proclamation''** means Labour proclamation No.1156/2019.
   2) **''Young worker''** means a natural person

የሞላውና 18 ዓመት ያልበለጠው ግለሰብ ነው፡፡

3. **“ተከታታይነት ያለው ሥራ”** ማለት የሥራው እንቅስቃሴ የመቋረጥ ባሕሪይ የሌለበት እና የድግግሞሽ ሂደት የሚታይበት ሆኖ አካላዊ ጫና የሚያስከትል እና ወጥነት ያለው የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡

4. **“አደገኛ ሥራዎች”** ማለት በባሕሪያቸው ለሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት አስጊ የሆኑ በጥሬ ዕቃነት፣ በተጨማሪ ግብአትነት፣ በምርትነትና በተረፈ ምርትነት የሚያገለግሉ ወይም በአሠራሩና በሥራው ሁኔታ የተነሳ የሚከሰቱ የአደጋና የጤና ጉዳት ስጋቶች ያሉባቸው ሥራዎችና የሥራ ዘርፎች ናቸው፡፡

5. **“አደገኛ ኬሚካሎችና ንጥረ ነገሮች”** ማለት ባላቸው ፊዚካላዊና ኬሚካላዊ ውህድ ንጥረ ነገር ይዘት በሰውና በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ቁሶች ናቸው፡፡

6. **“ከባድ ሥራ”** ማለት በደቂቃ ከ7.0 ኪሎ ካሎሪ በላይ የሆነ ሜታቦሊክ ኢነርጂ ወይም ጉልበት የሚጠይቅ የሥራ እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡

7. **“ከመሬት በታች የሚካሄድ የቁፋሮ ሥራ”** ማለት ከመሬት በታች በመሳሪያና በእጅ ከሚደረግ ጥልቅ የማዕድን

who has attained the age of 15 but is below the age of 18 years.

3) **“Continuous Work”** is uninterrupted and repetitious work that causes physical stress.

4) **“Dangerous Works” are** those which, by their nature, are hazardous to workers’ health and may involve raw materials, supplementary inputs, products, and residual products that are employed in the work process.

5) **“Dangerous Chemicals and Elements”** are those which, by the content of their physical and chemical compounds have negative impact on humans and on the environment.

6) **“Heavy Work”** is work that requires the exertion of 7.0 kilo calories per minute of metabolic energy.

7) **“Subterranean Excavation Work”** is work that is carried out underground by hand or machine and is related to mineral

ቁፋሮ፣ በኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ የሚደረግ ቁፋሮ እና የተያያዙ ሥራዎች ናቸው፡፡

8. “ጨረራ” ማለት ማንኛውም የውስጥ አካልና ህዋስን ሰንጥቆ የማለፍ ኃይል ያለው የኤሌክትሮ ማግኔትክ ሞገድ ነው፡፡

9. “የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ” ማለት በመከላከል መርህ ላይ የተመሰረተ፣ የሥራ ቦታዎች ምቹ፣ ጤናማና ከአደጋ የተጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ ጤናማ አምራች ዜጋ ለመፍጠርና የሥራ ውጤትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል የተደራጀ፣ በሥርዓት የሚመራና በቅንጅት የሚፈጸም የልማት እንቅስቃሴ ነው፡፡

10.”የሥራ አካባቢ“ ማለት ማንኛውም ሠራተኛ ለስራ የሚገኝበት እና በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በአሰሪው ቁጥጥር ሥር የሚገኝ የሥራ ቦታ ነው፡፡

11.አዋጁ አንቀፅ 2 ሥር የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

12.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 በሚሸፈኑ

extraction, construction works and related undertakings.

8) **“Radiation”** is any electromagnetic wave that has the power to pass through internal organs and tissues.

9) **“Occupational Safety and Health”** is based on the principle of prevention and aims at ensuring a convenient and healthy workplace in order to have a healthy and productive citizen capable of bringing about development that is organized and coordinated.

10) **“Workplace”** is that where workers are engaged in a job, and in a place, which is under the employer’s control directly or indirectly.

11) The definitions given in Article 2 of the Proclamation apply to this Directive.

12) Provisions of this directive set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

**4. <u>Scope of Application</u>**

This Directive shall be applicable to employers and young workers who are

አሠሪና ወጣት ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. **<u>ወጣት ሠራተኞች እንዳይሰማሩባቸው የተከለከሉ የሥራ ዘርፎች</u>**

የወጣት ሠራተኞችን ህይወት፣ ደህንነትና ጤንነት ለአደጋ የሚያጋልጡ ሥራዎች እና የስራ ዘርፎች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

1. መንገደኞችንና ዕቃዎችን በመንገድ፣ በአየርና ውሃ ላይ የማጓጓዝ እና ዓሳ የማስገር ሥራዎች መስራት፣
2. በወደቦችና በመጋዘኖች የሚሰራ ከባድ ዕቃዎችን የማንሣት፣ የመጎተት ወይም ከዚህ ጋር የተያያዙ የጉልበት ሥራዎች፣
3. ከኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች፣ ከኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና ከማከፋፈያ ጣቢያዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች፣
4. ከመሬት በታች በሚካሄዱ ጥልቅ የማዕድን ቁፋሮ፣ የድንጋይ ካባዎች እና የመሳሰሉ ሥራዎች መስራት፣
5. ከከፍታ ቦታ የኮንስትራክሽን ሥራ በርብራብ/ስካፎልዲንግ/ ላይ ሆኖ መሥራት፣ ዕቃን ከታች ወደ ላይ ወይም ከላይ ወደ ታች በመሣሪያ ተጠቅሞ ማንቀሳቀስ፣ በኤሌክትሪክ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱ ክሬኖችና ሊፍቶች በመጠቀም ዕቃን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ

governed byLabor Proclamation No.1156/2011.

5. **<u>Lists of Activities Prohibited for Young Workers</u>**

The following is a list of jobs that expose young workers to dangers to their lives, safety, and health.

1) Transporting persons and goods by land, air, and water; and fishing.
2) Lifting, pulling heavy goods or works related to these in ports and warehouses.
3) Works directly related to electric power generating stations, transmission lines, and power distribution centers.
4) Subterranean works like deep mineral extraction, stone quarries, or related works.
5) Work on high places on scaffoldings, moving materials up or down using machines, or moving materials from one place to another on cranes and lifts using electric or motorized energy.

የማንቀሳቀስ ሥራዎች፣

6. የአልኮል፣ የሲጋራ እና ሌሎች ሱስ ሊያስይዙ ወይም ሊመርዙ የሚችሉ ንጥረ ነገሮች ማምረቻ ፋብሪካዎች፤

6) Work in under takings that produce alcohol, tobacco or other substances that induce addiction or are poisonous.

7. በጣም ቀዝቃዛ በሆኑ ስራ አካባቢዎች፣ ማከማቻ መጋዘኖች፣ ማቀዝቀዣዎች እና የሥራ ክፍሎች ውስጥ መሰራት፣

7) Work in extremely cold places, warehouses, freezers.

8. ከፍተኛ የሙቀት ጫና ያለባቸው የሥራ አካባቢዎች ውስጥ መሥራት፣

8) Work in extremely hot places.

9. ጎጂ ለሆኑ የአዮናይዚንግና አዮናይዚንግ ያልሆኑ (የኤክስ ሬይ፣ አልትራቫዮሌት ሬይ፣ ጋማሬይ ወዘተ…) ጨረሮች የሚያጋልጡ ሥራዎችን መስራት፡

9) Jobs that expose young workers to harmful ionizing and non-ionizing radiations like x-rays, ultra-violet rays, gamma rays etc.

10. አደገኛና መርዘኛ የሆኑ ኬሚካሎችን ማለትም አርሴኒክ፣ ሊድ፣ ሜሪኩሪ፣ ካድሚየም፣ ማንጋኒዝ፣ ሳያናይድና የመሳሰሉ ብረታማ ንጥረ ነገሮችና አሚሚዎች ሥራ ላይ በሚውሉበት የሥራ ዘርፍ መስራት፣

10) Work in production areas that use dangerous and poisonous chemicals like arsenic, lead, cadmium, manganese, cyanide and other such metallic substances and solvents.

11. የተቀጣጣይነት እና የፈንጂነት ባህርይ ያላቸውን ውህዶች እና ንጥረ ነገሮች በሚመረቱባቸውና አገልግሎት ላይ በሚውሉባቸው

11) Works which produce or utilize explosive and incendiary substances and elements.

ሥራዎች ውስጥ መስራት፣

12. የተለያዩ የፀረ ተባይ እና የፀረ አረም ኬሚካሎች የማዘጋጀት፣ የመበጥበጥና የመርጨት፣ ሥራዎች

13. ተላላፊ በሽታዎችን የሚያስከትሉ ስነ ህይወታዊ ጠንቆች ማለትም ከፈንገስ፣ ከባክቴሪያና ቫይረስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች ላይ መስራት፡

14. ወጣቶችን አካላዊ፣ አዕምሯዊ እና ስነ ልቦናዊ ጉዳቶች ሊያደርሱ የሚችሉ ስራዎች ላይ መሰማራት፣

## 6. ለወጣት ሠራተኞች የተወሰነ የክብደት መጠን

ወጣት ሰራተኞች ተሰማርተው በሚገኙበት የስራ ዘርፍ አልያም በድንገተኛና የአጭር ጊዜ ስራዎች የወጣት ሠራተኞችን ጉልበት በመጠቀም የሚካሄድ ማናቸውም ክብደትን ከቦታ ቦታ የማንቀሳቀስ፣ የመሸከም፣ የማጓጓዝ፣ የማንሳት፣ የማውረድ፣ የማውጣት፣ የመጎተት፣ የመሳብና የመሳሰሉት ሥራዎች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን የክብደት መጠን ጣሪያ ሳያልፉ ይከናወናሉ፡፡

1. እንቅስቃሴው ሙሉ በሙሉ በእጅ ሆኖ፡-

ሀ/ ተከታታይነት ላለው ሥራ የዕቃው ክብደት እስከ 7

12) Jobs which involve preparation, mixing, or spraying of various pesticidal and herbicidal chemicals.

13) Jobs which bring the worker into direct contact with biological hazards like fungi, bacteria, and viruses that cause contagious diseases.

14) Jobs that can harm the physical, mental, and psychological well-being of young workers.

## 6. Weight Limits for Young Workers

Any job that uses young workers' labor, even sporadically and for a brief period, involving moving, carrying, transporting, lifting, loading, unloading, dragging, or pulling goods and materials shall not exceed the weight limits indicated below.

1) Where the activity is wholly manual:

   a. For continuous work: 7 kgs.

ኪሎ ግራም

ለ/ ተከታታይነት ለሌለው ሥራ
የዕቃው ክብደት እስከ 11 ኪሎ ግራም

2. እንቅስቃሴው ሙሉ በሙሉ በእጅ ሆኖ ዳገት የመውጣትና የመውረድ ሁኔታ ከታከለበት፡-

ሀ/ ተከታታይነት ላለው ሥራ
የዕቃው ክብደት እስከ 5 ኪሎ ግራም

ለ/ ተከታታይነት ለሌለው ሥራ
የዕቃው ክብደት እስከ 9 ኪሎ ግራም

3. እንቅስቃሴው ባለ አንድ እግር ጋሪ ሆኖ

ሀ/ ወለሉ ባልተስተካከለ ንጣፍ የዕቃው ክብደት እስከ 16 ኪሎ ግራም

ለ/ ወለሉ በተስተካከለ ንጣፍ የዕቃው ክብደት እስከ 20 ኪሎ ግራም

7. **<u>መመሪያው ተፈፃሚ የማይሆንባቸው የሥራ ዘርፎች</u>**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩ ሥራዎች ኃላፊነት የተሠጠው ባለሥልጣን ባፀደቀውና በሚቆጣጠረው የትምህርትና የሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት በሚሰለጥኑና ልምምድ በሚያደርጉ ወጣቶች ላይ

b. For non – continuous work: 11 kgs.

2) Where the activity is wholly manual, but involves climbing up and down a slope:

a. For continuous work: 5 kgs.

b. For non – continuous work: 9 kgs.

3) Where the movement is on a one-wheel barrow:

a. Where the floor is bumpy and not smooth: 16 kgs.

b. Where the floor is smooth: 20 kgs.

7. **<u>Work Activities Where the Directive is not Applicable.</u>**

The Directive shall not be applicable to Youth who are engaged in training and practice under educational and vocational institutions authorized and supervised by the given authority which have

መመሪያው ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

8. <u>ስለ ኃላፊነት</u>

ማንኛውም የአሰሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሊተገብር ይገባል፡-

ሀ. አሰሪዎች የወጣት ሠራተኞችን ቅድመ ቅጥር ማልመላን በተመለከተ ስለ እድሚያቸው የማረጋገጥና የማጣራት ስራ

ለ. ወጣት ሠራተኞች የተፈቀዱ ወይም የተከለከሉ የስራ ዝርዝሮችን ለድርጅቱ አስተዳደር ክፍልና ለመሰረታዊ ሰራተኛ ማህበርና ሴፍቲ ኮሚቴ ግንዛቤ መፍጠር

ሐ. የወጣቶችን ትክለኛነት በዚህ መመሪያ ክልከላ በተደረገባቸው ሥራዎችና የሥራ ዘርፎች ውስጥ የተሰማሩ ወጣት ሠራተኞች ካሉ ደመወዛቸው ሳይቀነስ ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ የማሰራትና የጤና ጉዳት ያለመከሰቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

መ. አሰሪው የወጣት ሠራተኞችን የሥራ ላይ አደጋ እና የጤና ጉዳትን ሁኔታ ለመከታተልና

responsibility on the activities listed under Article 5 of this Directive.

8. <u>**Responsibility**</u>

An employer has the following responsibilities:

a) To ascertain and verify the age of the pre-employment young worker recruits.

b) To create awareness in members of the undertaking's Administration Department and the Trade Union's Basic Safety Committee about the list of jobs that are permitted or prohibited for young workers.

c) To transfer entitled young workers engaged in works or branches of work that are prohibited for young workers in this Directive to other job assignments without any reduction in wages, and to ensure that they have not suffered from any harm to their health.

d) To undertake free pre-employment

ለማረጋገጥ ኤች.አይ.ቪ. ምርመራ በስተቀር ቅድመ ቅጥር የጤና ምርመራ በነጻ የማድረግና መረጃዎችን መያዝ

ሠ. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በሚኒስቴሩ / አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚሰጡ ትዕዛዞችን ተፈጻሚ ማድረግ አለበት፡፡

ረ. የመመሪያውን አፈፃፀም ለሚኒስቴሩ/አግባብ ላለው ባለስልጣን በየግማሽ ዓመት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

9. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም የሚመለከተው አካል ወይም ግለሰብ ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

10. <u>ቅጣት</u>

ይህ መመሪያ የሚመለከተው ማንኛውም አሠሪ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ ድንጋጌዎችን ቢጥስ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/11 ስለቅጣት የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡፡

health examination, except for HIV, and maintain the records in order to follow up on occupational injury and harm to health.

e) An employer should implement orders related to the Directive that are given by the Ministry or appropriate authority.

f) An employer should submit an implementation report to the Ministry or appropriate authority every six months.

**9. <u>Obligation to Cooperate</u>**

Any stakeholder, corporate or individual, has the duty to cooperate in the implementation of this Directive.

**10. <u>Penalty</u>**

Any employer that contravenes the regulations listed in this Directive shall be subject to the penalties decreed in Labor Proclamation No.1156/2011.

**11. መመሪያውን ስለ ማሻሻል**

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የዚህን መመሪያ አፈፃፀም በየወቅቱ እየገመገመ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**12. የተሻረ መመሪያ**

ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች ዝርዝር ለመወሰን ከሚያዝያ 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የወጣው መመሪያ ተሽሯል፡፡

**13. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ነሐሴ 18 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)

የሠራኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር

**11. Modification of the Directive**

The Ministry may periodically assess the implementation of this Directive and modify it.

**12. Repealed Directive**

The Directive issued in April 2013 on the Lists of Activities prohibited for young workers is hereby repealed.

**13. Effective date of the Directive**

This Directive shall be in effect from the date of signing by the Minster on 24 August, 2021.

Addis Ababa

Ergogie Tesfaye (PhD)

Minister of

The Ministry of Labour and Social Affairs